# የዲያስፖራ ፖለቲካና ጽንፈኝነት…!

ክፍል ሁለት
ገረመው

ትግራይ ኦንላይን April 19, 2014

ፅንፈኛው ዲያስፖራ ከደርግ ውድቀት በኋላም ይበልጥ እየተጠናከረ የሄደ መሰለው፡፡ ብዛት ያላቸው የደርግ ካድሬዎች፣ የጦር መኮንኖች፣ ከያንያን፣ እና የትምክህት ፖለቲካ አራማጅ ምሁራን ተሰደው ከፅንፈኛው ጎራ ተቀላቀሉ፡፡

በደርግ ዘመን ከፍተኛ ቦታ ይዘው የነበሩ ካድሬዎች በተራቸው ተሰደዱ፡፡ በሠላም ጉባኤ ስም በፓሪስና በሌሎች ከተሞች ሥልጣን ናፋቂ ሁሉ የተጠራራበት ጉባኤዎች ተካሄዱ፡፡ አልፈው ተርፈው እስከ ግዮን ሆቴል ድረስ በመሄድ የፖለቲካ አክሮባት በመሥራት የእርስዎም ይሞክሩት ጨዋታ ሞከሩ፡፡

ይህ ሲሆን ብዙሀኑ የዲያስፖራው አባላት በአገር ቤት በመካሄድ ላይ ለነበረው የዴሞክራሲ ፖለቲካ ድጋፍ ሰጡ፡፡ ድጋፉን ቀጥታዊና ቀጥተኛ ያልሆነ በሚል መግለፅ ይቻላል፡፡ ብዙሀኑ የዲያስፖራ አባላት የፅንፈኞችን ፖለቲካ በመቃወም ከመንግሥትና ከአገራቸው ጋር ያላቸውን ግንኙነት ሠላማዊ ይሆን ዘንድ መረጡ፡፡ የብዙሀኑ ፍላጎት አገራቸው እፎይታ አግኝታ የሕዝቡ ኑሮ እንዲሻሻል ነው፡፡ በሥልጣን ላይ ያለው ፓርቲ የሚከተለውን ፖሊሲ ሙሉ በሙሉ ባይደግፉም በሠላም፣ በልማትና በዴሞክራሲ ላይ አጠቃላይ መግባባት ላይ ደረሱ፡፡

የፅንፈኛው ክልከላና እግድ ቁብ ሳይቆጥሩ በዓል በመጣ ቁጥር አገራቸው ገቡ፡፡ ሌላው ክፋይ ቀጥተኛ ድጋፍ የሰጠ ሲሆን ይህም ፅንፈኞችን በቀጥታ በመታገል የሚገለፅ ነው፡፡ ብዛት ያላቸው የዲያስፖራ አባላት በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያና በአካል ቀጥተኛ ድጋፍ ይሰጡ ያዙ፡፡ በሂደትም ፅንፈኞች እየተነጠሉ ሄዱ፡፡ የዲያስፖራው ፅንፈኞች ተነጥለው አድማጭም አጥተው ማላዘን በጀመሩበት ወቅት የ1997 ዓ.ም ምርጫ ደረሰ፡፡
ምርጫ 97 ለሁሉም ተፋላሚ ቡድኖች ልዩ ትርጉም ነበረው፡፡ ገዥው ፓርቲ እንከን የለሽ ምርጫ ያካሂድ ዘንድ ቃል ገባ፡፡ ፅንፈኛ ቡድኖች በበኩላቸው ወደ ምርጫ የሚገቡት ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን ለመናድ መሆኑን አሳወቁ፡፡ ለዚሁም ይበጃል ያሉት ኋላ ቀርና ዘረኛ ቅስቀሳቸውን ዘረገፉት፡፡

የሕዝቦች የመቻቻልና የአብሮነት ባህል የሚፈታተኑ ቅስቀሳዎች አራመዱ፡፡ የዲያስፖራው ፅንፈኛም ተስፋ ሰንቆ የዘረኝነት ከበሮውን ለጆሮ እስኪሰቀጥጥ ድረስ አስጮኸው፡፡ በአገራችን ቋንቋዎች የሚሰራጩ የባዕድ ራዲዮ ጣቢያዎችም በእሣት ላይ ቤንዚን አርከፈከፉ፡፡ አንዳንድ ለፖለቲካ ደንታ ያልነበራቸው የዲያስፖራ ባለሀብቶችና ወይዛዝርትም ጥሪታቸውን ቅንጅት ለተባለው ቡድን ግብር አገቡ፡፡ ባህር ማዶ ሆነው አገር ቤት እሣት እንዲቀጣጠል ወተወቱ፡፡

ምርጫ 97 በአገር ቤትም ይሁን በዲያስፖራው የተኛውን አጋንንት ጭምር ቀሰቀሰ፡፡ አቶ አስማማው ኃይሉ "ከጎንደር - ደንቢያ  እስከ ዋሽንግተን ዲሲ ቁጥር 2" በሚለው መፅሐፋቸው ላይ የወቅቱን ሁኔታ ሲገልፁ "ወቅቱ አስተዛዛቢ ሆነ፣ ከዚህ ቀደም ስለአገራቸው የፖለቲካ ሁኔታ ለሰኮንድም ተጨንቀው የማያውቁ ግለሰቦች በቅንጅት ድርጅታዊ ሰልፍ በመጀመሪያ ረድፍ ለመቆም እሽቅድምድም ያዙ፡፡ አንዳንድ ቱጃሮችም መጠነ ሰፊ የገንዘብ እርዳታ በመለገስ ያዲሱ መንግሥት የበኩር ልጅ ለመሆን ከማንም በላይ ገዝፈውና ረዝመው ታዩ" ይሉናል፡፡

የዲያስፖራው የፖለቲካ ልሂቃን ከምርጫው ዋዜማ አስቀድመው ተቃዋሚ ወገን ወደ ምርጫ የሚገባው የፓርላማ ወንበር ለማሞቅ ሳይሆን በቅድመ ምርጫ ዘመቻ ደጋፊዎችን በማሰባሰብ የምርጫ ውጤት ተጭበርብሯል በሚል ሽፋን የጎዳና ላይ ነውጥ ለማካሄድ እንደሆነ የቀድሞ የመኢሶን የቀይ ሽብር መሐንዲስ በአዲስ ዘመን የጎዳና ላይ ነውጥ የርዕዮተ ዓለም መሪ በመሆን አቅጣጫ አስቀመጡ፡፡ ከፓሪሱ የሠላም ጉባኤ ጀምሮ ዴሞክራሲያዊ ሕብረት የተባለው ቡድንም የዲያስፖራ ፖለቲካ ልሂቃን ፈረስ ሆኖ ሲያገለግል የነበረው ይህንን አጀንዳ አንግቦ ወደ ምርጫ ገባ፡፡

በምርጫው ወቅት ሕብረተሰቡ በደረሰበት የመልካም አስተዳደር እጥረት ኢሕአዴግን በድምፅ ለመቅጣት ፊሽካ አሰማ፡፡ ይህን የተመለከቱ ችኩል የዲያስፖራ ልሂቃንም የተመኙት ጊዜ የደረሰ መሰላቸው፡፡ የዛለ ጉልበታቸውን

ማፍታታት ያዙ፡፡ በ97 ምርጫ የኢትዮጵያ ሰፊ አርሶ አደር ኢሕአዴግ የቀመረውን ሠላምና የልማት ሂደት እንዳይቀለበስ በድምፁ አገሩን ታደገ፡፡ አሁንም አቶ አስማማው ኃይሉ “በሰሜን አሜሪካ ከምንኖረው አንዳንድ ፖለቲከኞች ነን ባዮች ይልቅ የኢትዮጵያ አርሶ አደር ብስለት የላቀ እንደሆነ ተገነዘብን” ይሉናል፡፡

የዲያስፖራ ልሂቃን የጎዳና ላይ አመፅ በማስተጋባት በምርጫው ተሳትፈው የፓርላማ ወንበር ያገኙ ወገኖች ወደ ፓርላማ እንዳይገቡ በሩን ጥርቅም አድርገው ዘጉ፡፡ ይህም የሆነው በአገር ቤትና በዲያስፖራ በሚገኙት ፅንፈኞች ቅንጅት በመፍጠር ነበር፡፡ የቅንጅት መሪ የነበሩት በፅንፈኛው ዲያስፖራ መሀል ሆነው ቤተ መንግሥት ለመያዝ ቢያንስ 15 ሺህ ህይወት መክፈል የግድ እንደሚል ተነበዩ፡፡

በዚሁም ብዙ ሙገሳ አተረፉ፡፡ ለፓርላማ ተወዳድረው መቀመጫ ካገኙ በኋላ ተመልሰው የመረጣቸውን ወገን ፓርላማ እንግባ ወይ ብለው በመጠየቅ የአገራችን ተቃዋሚዎች በዓለማችን የመጀመሪያዎቹ ሆኑ፡፡ ፅንፈኛው ዲያስፖራም ፓርላማ መግባት እንደሌለባቸው ወሰነ፡፡ በሂደትም የድርጅቱ የፋይናንስ ምንጭ የነበረው ዲያስፖራ ቡድን አሸነፈ፡፡

የዲያስፖራው ልሂቃን ሠላማዊ የፖለቲካ ሂደት ትተው አመፅን አበረታቱ፡፡ ሰው በዕድሜ እየገፋ ሲሄድ በአገርኛ አባባል አስታራቂና ሽማግሌ ይሆናል እንጂ 70ቹ ተደርሶ ጦርነት ማወጅ ተገቢ አይሆንም፡፡ የዲያስፖራው ፅንፈኛ የአገር ቤቱ መንግሥት ሙሉ በሙሉ ፈርሶ ከዜሮ መጀመርን ይመርጣል፡፡ የአገር ቤት ሀብትና ንብረት ሊቆጣጠሩ ከሆነ የግድ መንግሥትንና በሥራ ላይ ያሉ ሕጎችን በሙሉ በመናድ ማስወገድ አለባቸው፡፡

ይህ በሠላማዊ ፖለቲካ ሂደት ሊሳካ የሚችል አይደለም፡፡ ለእነሱ በሥራ ላይ ያለው ሕገ መንግሥትና ሌሎች ሕጎች ከወጣላቸው ቀለም በላይ ዋጋ የላቸውም፡፡ ለነገሩ በተለያዩ ጊዜያት በሕዝብ ላይ ጥፋት ፈፅመው የተሰደዱ ስለሆኑ ሕግና ሥርዓት እንዲፈርስ መሟገታቸው የሚገርም አይደለም፡፡ ይህ ደግሞ የዘመናችን የኒዮ ሊበራሎች አስተሳሰብም ጭምር ነው፡፡ ሁሉንም ነገር ከዜሮ መጀመር፡፡

የዲያስፖራው የፅንፈኞች ልሂቃን በአሁኑ ወቅትም ቢሆን ተመልሰው አገር ለመቆጣጠር ያስችለናል ያሉትን አደረጃጀት ፈጥረዋል፡፡ የሽግግር መንግሥት፣ የቴሌቪዥን ጣቢያ፣ ራዲዮ፣ የቤተክህነት ተቋማት፣ የትጥቅ ትግል ወዘተ መነሻቸው ሁሉንም ነገር ከዜሮ የመጀመር ህልም፡፡

የዲያስፖራ ፅንፈኞች በ97ቱ የፖለቲካ ምርጫ ላይ ሲሳተፉ በነበሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች ላይ ከፍተኛ ጫና ቢያሳድሩም ቅንጅት የተባለው ስብስብ አነስተኛ ክፋይ በስተቀር ሌሎች ቡድኖች ወደ ፓርላማ ተቀላቀሉ፡፡

ዴሞክራሲያዊ ሕብረት የተባለው ቡድን  ፅንፈኛው ዲያስፖራ የወጠነው የጎዳና ላይ ነውጥ ባለልቼንሳ የነበረ ቢሆንም መንገዱ እየጠጠረ ሲሄድ የነውጡን አጀንዳ ለቅንጅት አስረክቦ ወደ ፓርላማ ገባ፡፡

የአራት ኪሎ ቤተ መንግሥት በ15 ሺህዎች ደም ለመቆጣጠር የቋመጡ የቅንጅት ፅንፈኞችም በዲያስፖራው ፅንፈኛ እየተነዱ ወህኒ ወረዱ፡፡ የወህኒ ኑሮ የተመኙት ባለመሆኑ ምሕረት ጠይቀው ከእሥር ሲለቀቁ የዲያስፖራው ፅንፈኛ አንገቱን መድፋት ጀመረ፡፡

ፅንፈኛው ፍላጎት ሕጋዊ ሥርዓቱን የሚጋፋና የሚፈታተን እንጂ የአገሩን የፍትሕ ሥርዓት ተከትሎ መሄድ ለእነሱ ውርደት ነው፡፡ የጀግኖች ተምሣሌት ተደርገው ሲታዩ የነበሩ አንዳንድ ብልጣብልጥ የቅንጅት ነባር መሪዎችም በሀሳብ ከወጡበት ማማ መውረዳቸውን ሲረዱ ወደ ሥደት በመሄድ “ሆ ብዬ መጣሁ” በማለት ፅንፈኛውን ዳግም አስጨፈሩት፡፡ የጭፈራውን ሙቀት የተመለከተው ዶክተር ብርሃኑ ነጋም አሁንም ከእያንዳንዱ ሰው 500 ዶላር ከተዋጣለት በአጭር ጊዜ ውስጥ መንግሥት መገልበጥ እንደሚችል ይፋ አደረገ፡፡ ተስፈኛው ፅንፈኛም ከምርጫ 97 የቀረችውን ጥሪት ለብርሃኑ ነጋ ግብር አስገባ፡፡

ግንቦት 7 የተባለ የብርሃኑ ነጋ ኩባንያ ሁሉም ዓይነት የትግል ሥልት በመጠቀም በሕዝብ የተመረጠውን መንግሥት ለመጣል አሥመራ ወረደ፡፡ “የክረምት ሙጃ መስከረምን አያልፍም” እንዲሉ ከአራት ዓመት በኋላ የሰማነው ነገር ቢኖር “በኤርትራ አንድ ጋንታ እያሰለጠንኩኝ ነኝ”፣ የሚል እና ከአገራችን ታሪካዊ ጠላቶች “500 ሺህ ዶላር” ማግኘቱን ነው፡፡

በዘመናችን ፖለቲካ ብርሃኑ ነጋን የሚያህል ብልጣ ብልጥ አራዳ ነጋዴ ታይቶም ተሰምቶም አይታወቅም፡፡ አቶ በረከት ስምኦን “የሁለት ምርጫዎች ወግ” ብለው በሰየሙት መፅሐፋቸው ላይ ብርሃኑ ነጋ በቅድመ ምርጫ 97 ቅንጅት በጠራው ትልቅ ሰልፍ ላይ አለመሳተፉንና በዕለቱ ከአዲስ አበባ ወጣ ብሎ እንዳሳለፈ ይገልፃል፡፡

የዶክተር ብርሃኑ ሌላው ታሪክ የ97 የጎዳና ላይ ነውጥ ምክንያት ከታሰረ በኋላ የቅንጅት አመራሮች በጋራ ምሕረት እንዲጠይቁ ግንባር ቀደም ሆኖ ሲገፋ የነበረ ሰው እንደሆነ ብዙዎቹ መስክረዋል፡፡

ሌሎች የኢትዮጵያ ወጣቶች ደርግን ለመጣል መሣሪያ አንስተው ወደ በረሃ ሲወጡ ብርሀኑ ነጋ ቁርና ሀሩሩን ለመሸከም ስለማይችል ወደ ውጭ አገር ተሰዶ ኑሮውን ሲገፋ ቆይቶ ደርግ ሲወድቅ አገር ቤት የተመለሰ ግለሰብ መሆኑ ነው፡፡ ከእሥር ቤት ተለቆ ወደ ውጭ ከወጣ በኋላም ይህን የራሱን ታሪክ በመካድ ዲሞትፎር ታጥቆ መንግሥት ለመጣል ከጀለው፡፡ ወጣም ወረደም ፀረ ደርግ ነበርኩ የሚል ወገን መሣሪያ አንስቶ በሥልጣን ባለው መንግሥት ላይ ጦር መስበቅ የሞራል ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

የዲያስፖራው ፅንፈኛ በአሁኑ ወቅት ተስፋ የቆረጠበት ደረጃ ላይ የሚገኝ ቢሆንም ሸንፈት ሲያጋጥም አፈገፈግን የሚሉ የአሥመራ አማካሪዎች ስላሏቸው ያፈገፈጉ ይመስላሉ፡፡

የአገር ቤት የልማት ፍጥነትም አዳፍኔ ሆኖባቸዋል፡፡ ሁኔታዎችን ልብ ብለን ስንመለከት አሥር የስኳር ፋብሪካዎች ይገነባሉ ሲባል የዋልድባ ገዳም ፈረሰ ብለው ኡኡታ ለቀቁ፤ የአዲስ አበባ ባቡር መንገድ ሲጀመር አቡነ ጴጥሮስ ሀውልት ፈረሰ ብለው ሰልፍ ወጡ፤ ታላቁ የህዳሴ ግድብ ግንባታ ተጀመረ ሲሏቸውም ለገዥው ፓርቲ ጥቅም ነው በማለት ቀሰቀሱ፤ ኢትዮጵያ በሁለት አሀዝ አደገች ሲባል የቁጥር ጨዋታ ነው ብለው ተሚገቱ፤ አንዳንዶቹ የግብፅ ሙርሲ የአባይን ውሃ የነካ ወዮለት ሲል ሳይደግስ አይጣላም በማለት ጮቤ ረገጡ፡፡ መንግሥት ግን ግመሉ ይሄዳል፤ ውሾች ይጮሀሉ በማለት ጉዞውን ቀጠለ፡፡

በዲያስፖራ ያለውን ፅንፈኛ አመጣጥ በግርድፍም ቢሆን ተመልክተናል፡፡ የዲያስፖራው ፅንፈኛ ከአገር ቤት ፅንፈኛ ጋር የዓላማና የትግል ሥልት ልዩነት የላቸውም፡፡ ከዚህ አንፃር የተወሰኑ ገዥ ባሕርያት አንጥረን በማጠቃለያ መልክ ማውጣት ይቻላል፡፡

አንዳንድ ምግብ ቤት ያላቸው ኢትዮጵያውያን ቤተሰብ ለመጠየቅ አገር ቤት በመሄዳቸው ብቻ አድማ በማስነሳት ምግብ ቤቱ እንዲከስር የተደረገበት ሁኔታ አሜሪካ የሚኖሩ ወገኖቼ ነግረውኛል፡፡ ሼሕ አላሙዲ ይደግፉታል በተባለው የአሜሪካ ኢትዮጵያውያን የእግር ኳስ ጨዋታ ላይ የተገኙ ከያንያን ከሕብረተሰቡ ለመነጠል ቅስቀሳ ሲካሄድ እኔም ራሴ ታዝቤያለሁ፡፡ አንድ ወቅት አንድ የአውሮፓ ፅንፈኛ አገር ቤት ደርሶ የተመለሰ ጓደኛውን ሆዳም በማለት እንደተጣላው ራሴም ምስክር ነኝ፡፡ የሚገርመው ነገር ደግሞ ፅንፈኞች አገር ቤት ደበቅ ብለው በመሄድ ቤትና ንብረት በማፍራት የሚቀድማቸው የለም፡፡ ለጥቅም ሲሆንማ ማን ብሏቸው!

ይህን ዕለታዊ ገጠመኝ መጥቀስ አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት የፖለቲካ ልዩነት ቀርቶ በግል ደረጃ እነሱ የሚሉትን ያላዳመጠውን ሁሉ ስም በመለጠፍ እንዲነጠል የማድረግ ፅንፈኞች የተካኑበት ሥልት መሆኑ ነው፡፡

ቀድሞ ነገር ፅንፈኛ ማለት የራሱን አስተሳሰብ በሌሎች ላይ በኃይል ለመጫን የሚሞክርና ከልዩነት ጋር አብሮ መኖር የተሳነው ማለት ነው፡፡ በምዕራቡ ዓለም ስንኖር ቢያንስ በአካባቢያችን መቻቻልን በቀላሉ መማር በቻልን ነበር፡፡ ነገር ግን ህሊናቸው ለዚህ ባለመፍቀዱ የማይረጥቡ ድንጋዮች ሆነው ቀርተዋል፡፡

ዴሞክራሲ ልዩነትን በአንድነት በሠላማዊ የፖለቲካ ትግል እያስታረቁ አገራችንም እየታደሰች የሚገጥሟትን አዳዲስ ፈተናዎች እንድትሻገር ማስቻል ነው፡፡ በአገራችን ዴሞክራሲና የመቻቻል ሥርዓት የማስፈን ጉዳይ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን የማስቀጠል ዝግጁነት ነው፡፡

ይህም ልዩነትን በአንድነት የሚለውን መርህ መከተል የግድ ይለናል፡፡ የግለሰብ መብት ማክበር ከብሔር፣ ብሔረሰብና ህዝብ መብት ጋር አንድ አካልና አምሳል እንጂ ተነጥሎ የሚታይ አይደለም፡፡ አገራችን የብዝሀነት ማዕከል በመሆኗ ከዚህ ውጭ ሌላ አማራጭ ስለመኖሩ እርግጠኛ አይደለሁም፡፡

ፅንፈኛፈው ዲያስፖራ ከማይመስለው ቀርቶ በውስጡም ስምምነት የለውም፡፡ በዲያስፖራው አካባቢ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተመሰረቱ ዜና ሳናጣጥም ፈረሱ የሚል ዜና ይሰማል፡፡ አንዳንድ ወገኖች ተቃዋሚዎች አንድ ሁኑ ወይም

ተሰባበሩ የሚል መልዕክት ሲያስተላልፉ ያልተረዳው ነገር ፅንፈኞች ከማንኛውም ወገን ጋር አንድነት ሊፈጥሩ የማይችሉ መሆኑን ነው፡፡